የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፶፮
አዲስ አበባ ነሐሴ ፰ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No. 56
ADDIS ABABA, 14th August, 2024

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፵፪/፪ሺ፲፮
የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት (ማሻሻያ) አዋጅ……..…….....ገጽ ፲፩ሺ፯፻፺፩

Content

Proclamation No.1342/2024
Export Trade Duty Incentive Schemes (Amendment) Proclamation ….....…..Page 15791

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፵፪/፪ሺ፲፮

የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፯፻፷፰/፪ሺ፬ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚዎች ሥርዓቱን ተጠቅመው ወደ ሀገር ያስገቡትን ጥሬእቃ ለምርት ተግባር አውለው ምርቱን በአንድ ዓመት ወይም በጉምሩክ ኮሚሽን በሚፈቅድላቸው ተጨማሪ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለዓለም አቀፍ ገበያ ማቅረብ ያለባቸው መሆኑ በአዋጁ የተደነገገ ቢሆንም፤ የዓለም አቀፍ ገበያ በመቀዝቀዙ ምክንያት ያመረቱትን ምርት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ያልቻሉ በመሆኑ፤

በበቂ ምክንያት በአዋጁ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ወደ ሀገር ባስገቡት ጥሬእቃ ምርት ማምረት እና ያመረቱትን ምርት ወደ ውጭ መላክ ያልቻሉ የማበረታቻ ሥርዓቱ ተጠቃሚዎች በጥሬ እቃው ምርት አምርተው ወደ ውጭ ሀገር ላለመላክ ምክንያት የሆነው ችግር እስከሚወገድ ድረስ በጉምሩክ ኮሚሽን አማካኝነት የጊዜ ገደቡ እንዲራዘምላቸው ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፤

PROCLAMATION No. 1342/2024

A PROCLAMATION TO AMEND EXPORT TRADE DUTY INCENTIVE SCHEMES PROCLAMATION No.768/2011

WHEREAS, beneficiaries of the export trade incentive schemes are unable to adequately produce and export their products due to the slow-down of the international market; although the Proclamation provides that beneficiaries are required to utilize raw materials imported into the country through the schemes for production purposes and avail the products to the international market within One year or an additional One-year period allowed by the Customs Commission;

WHEREAS, it is believed that beneficiaries who are unable to produce and export their products within the period prescribed by the Proclamation for sufficient reasons, shall be granted extension of time by the Customs Commission until the time the problem that caused delay in the production and export of the product is eliminated;

https://t.me/customsclearingagents

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፵፪/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. <u>ማሻሻያ</u>

የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፯፻፶፯/፪ሺ፬ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፦

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፪)ተሠርዟል።

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ ፫፣ ፬ እና ፭ ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፫፣ ፬ እና ፭ ተተክተዋል፦

"፫/ በቫውቸር ሥርዓት ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ጥሬ ዕቃ ለተጠቃሚው ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ምርት ተመርቶበት ምርቱ ለውጭ ገበያ መቅረብ አለበት፤ ሆኖም የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን በጥሬ ዕቃው ምርት ተመርቶበት ምርቱ ለውጭ ገበያ እንዲቀርብ ማድረግ ያልተቻለው በበቂ ምክንያት መሆኑን ሲያምንበት ይህንን የጊዜ ገደብ ለተጨማሪ አንድ ዓመት እና እንደ ሁኔታው ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል።

፬/ ማንኛውም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተው የጊዜ ገደብ እንዲራዘምለት የሚፈልግ የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ማመልከቻውን የጊዜ ገደቡ ከመጠናቀቁ በፊት ለጉምሩክ ኮሚሽን ማቅረብ አለበት።

፭/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የመጠቀሚያው የጊዜ ገደብ እንዲራዘም ወይም በአዋጁ አንቀፅ ፳፭ መሠረት ቀረጥና ታክሱን ከፍሎ በሀገር ውስጥ እንዲሸጥ ያልተፈቀደለት የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ጥቅም ላይ ባልዋለው ጥሬ ዕቃ ላይ ሊከፈል

NOW THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Article (1) and (11) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as the "Export Trade Duty Incentive Schemes (Amendment) Proclamation No 1342/2024."

2. <u>Amendment</u>

The Export Trade Duty Incentive Schemes Proclamation has been amended as follows :

1/Article 9 Sub Article (2) of the Proclamation is deleted.

2/ Article 10 Sub-Article 3, 4 and 5 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new Sub-Article 3, 4 and 5:

"3/ Raw materials imported under the voucher scheme shall be used in the production of export commodity and the commodity so produced shall be exported within One year from receipt of such raw materials by the beneficiary; provided, however, that when the Ethiopian Customs Commission believes that there is a sufficient reason for failing to export the production, it may extend this time limit until the reason is removed.

4/ A beneficiary of the voucher scheme desiring extension of the period stipulated in Sub-Article (3) of this Article shall be required to submit his application for extension to the Ethiopian Customs Commission before the expiry of the period.

5/ A beneficiary of the voucher scheme who has not secured permission for extension of the period stipulated under Sub-Article (3) of this Article, or to sell raw materials imported under this scheme upon payment

https://t.me/customsclearingagents

የሚገባውን ቀረጥና ታክስ በተጨማሪም የቀረጥና ታክሱን ሒሳብ ፲ በመቶ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡”

of duty chargeable on such raw materials in accordance with Article 25 of this Proclamation shall, in addition to the duty payable on the unused amount of the raw material, be required to pay 10% of the duty.”

፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ ፫፣ ፬ እና ፭ ተሠርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፫፣ ፬ እና ፭ ተተክተዋል፡-

“፫/ በቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ጥሬ ዕቃ ለተጠቃሚው ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ምርት ተመርቶበት ምርቱ ለውጭ ገበያ መቅረብ አለበት፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን በጥሬ ዕቃው ምርት ተመርቶበት ምርቱ ለውጭ ገበያ እንዲቀርብ ማድረግ ያልተቻለው በበቂ ምክንያት መሆኑን ሲያምንበት ይህንን የጊዜ ገደብ ለተጨማሪ አንድ ዓመት ወይም እንደ ሁኔታው ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል፡፡

3/ Article 12 Sub-Article 3, 4 and 5 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new Sub-Article 3, 4 and 5:

“3/ Raw materials imported under the bonded warehouse scheme shall be used in the production of export commodity and the commodity so produced shall be exported within One year from receipt of such raw materials by the beneficiary provided. However, that the Ethiopian Customs Commission may extend this time limit for One year or more as the case may be, when it believes that it is not possible to export the product using the raw material to the export market for a sufficient reason.

፬/ ማንኛውም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተው የጊዜ ገደብ እንዲራዘምለት የሚፈልግ የሥርዓቱ ተጠቃሚ የጊዜ ገደቡ ከመጠናቀቁ በፊት ማመልከቻውን ለጉምሩክ ኮሚሽን ማቅረብ አለበት፡፡

4/ A beneficiary of the bonded warehouse scheme desiring extension of the period stipulated in Sub-Article (3) of this Article shall be required to submit his application for extension to the Ethiopian Customs Commission before the expiry of the period.

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የመጠቀሚያው የጊዜ ገደብ እንዲራዘም ወይም በአዋጁ አንቀጽ ፳፭ መሠረት ቀረጥና ታክሱን ከፍሎ በሀገር ውስጥ እንዲሸጥ ያልተፈቀደለት የሥርዓቱ ተጠቃሚ ጥቅም ላይ ባልዋለው ጥሬ ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ በተጨማሪም የቀረጥና ታክሱን ፲ በመቶ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡”

5/ A beneficiary of the bonded warehouse scheme who has not secured permission for extension of the period stipulated under Sub-Article (3) of this Article, or to sell raw materials imported under this scheme upon payment of duty chargeable on such raw materials in accordance with Article 25 of this Proclamation shall, in addition to the duty payable on the unused amount of the raw material, be required to

https://t.me/customsclearingagents

፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ ፫፣ ፬ እና ፭ ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፫፣፬ እና ፭ ተተክተዋል፡-

“፫/ በቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ስርዓት ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ጥሬ ዕቃ ለተጠቃሚው ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ምርት ተመርቶበት ምርቱ ለውጭ ገበያ መቅረብ አለበት፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን በጥሬ ዕቃው ምርት ተመርቶበት ምርቱ ለውጭ ገበያ እንዲቀርብ ማድረግ ያልተቻለው በበቂ ምክንያት መሆኑን ሲያምንበት ይህንን የጊዜ ገደብ ለተጨማሪ አንድ ዓመት ወይም እንደ ሁኔታው ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል፡፡

፬/ ማንኛውም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተው የጊዜ ገደብ እንዲራዘምለት የሚፈልግ የሥርዓቱ ተጠቃሚ ማመልከቻውን የጊዜ ገደቡ ከመጠናቀቁ በፊት ለጉምሩክ ኮሚሽን ማቅረብ አለበት፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የመጠቀሚያው የጊዜ ገደብ እንዲራዘም ወይም አዋጁ አንቀጽ ፳፭ መሠረት ቀረጥና ታክሱን ከፍሎ በሀገር ውስጥ እንዲሸጥ ያልተፈቀደለት የሥርዓቱ ተጠቃሚ ጥቅም ላይ ባልዋለው ጥሬ ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ በተጨማሪም የቀረጥና ታክሱን ሒሳብ ፲ በመቶ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡”

pay 10% of the duty.’’

4/ Article 15 Sub-Article 3, 4 and 5 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new Sub-Article 3, 4 and 5:

“3/ Raw materials imported under the bonded export manufacturing warehouse scheme shall be used in the production of export commodity and the commodity so produced shall be exported within one year from receipt of such raw materials by the beneficiary; provided, however that the Ethiopian Customs Commission may extend this time limit for one year or more as the case may be, when it believes that it is not possible to export the product using the raw material to the export market for a sufficient reason.

4/ A beneficiary of the bonded export manufacturing warehouse scheme desiring extension of the period stipulated in Sub-Article (3) of this Article shall be required to submit his application for extension to the Ethiopian Customs Commission before the expiry of the period.

5/ A beneficiary of the bonded export manufacturing warehouse scheme who has not secured permission for extension of the period stipulated under Sub-Article (3) of this Article, or to sell raw materials imported under this scheme upon payment of duty chargeable on such raw materials in accordance with Article 25 of this Proclamation shall, in addition to the duty payable on the unused amount of the raw material, be required to pay 10% of the duty.”

https://t.me/customsclearingagents

፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተተክቷል፡-

"፫/ በቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ግብዓት ወደ መጋዘን ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለአምራች ካልተላለፈ የሥርዓቱ ተጠቃሚ በጥሬእቃው ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ እና በተጨማሪም የቀረጥና ታክሱን ፲ በመቶ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የጥሬ ዕቃው ለተጠቃሚው ማስተላለፍ ያልተቻለው በበቂ ምክንያት መሆኑን ሲያምንበት ይህንን የጊዜ ገደብ ለተጨማሪ አንድ ዓመት እና እንደ ሁኔታው ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል፡፡"

፯/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፰ ስር የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፲፱ ተጨምሯል፡፡ በ አዋጁ አዲስ አንቀጽ ፲፱ በመጨመሩ ምክኒያት፣ ከ አንቀጽ ፲፱ ጀምሮ ያሉት ድንጋጌዎች በ ቅደም ተከተል ከአንቀጽ ፳ እስከ አንቀጽ ፴፬ በመሆን ተሸጋሽገዋል፡፡

"፲፱. <u>በዱቤ ወይም በፍራንኮ ቫሉታ ጥሬ ዕቃ ስለማስመጣት</u>

የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ ጥሬ ዕቃዎችን አቅራቢዎች በሚሰጡት ዱቤ ወይም በፍራንኮ ቫሉታ ወደ አገር የሚያስገባ ከሆነ፡-

ሀ) ተፈላጊው ምርት በ ሀገር ውስጥ ከተመረተ በኋላ የምርቱ ተቀባይ መኖሩን የሚያረጋግጥ ከገዥው የተላከ ትዕዛዝ ወይም ከገዥው ጋር የተደረገ ውል ማቅረብ የሚችል፤ ወይም

ለ) ጥሬ ዕቃው የወጪ ምርቶችን ለማምረት ውጭ ሀገር ከሚገኝ ተባባሪ ኩባንያ የተላከለት መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት፡፡"

5/ Article 18 Sub-Article (3) is deleted and replaced by the following new Sub-Article (3):

"3/ If input supplies imported under the bonded input supplies warehouse scheme is not delivered to a producer within one year of being transferred into a bonded supplies input warehouse, the beneficiary shall, in addition to the duty payable on the input supplies, be required to pay 10% of the duty provided. However, that the Ethiopian Customs Commission may extend this time limit for one year or more as the case may be, when it believes that it is not possible to export the product using the raw material to the export market for a sufficient reason.

6/ The following new Article 19 has been added next to Article 18 of the Proclamation. As a result Article 19 and subsequent Articles of the Proclamation are amended as Articles 20-34 respectively.

"19. <u>Import of raw materials on Suppliers credit or franco-valuta</u>

If a beneficiary of the scheme imports raw materials on supplier's credit or franco-valuta, he is required to submit evidence confirming that:

a) the commodity has demand and that the demand is confirmed by a purchase order issued by the prospective buyer or submit a purchase agreement concluded with the prospective buyer; or

b) the raw materials are sent by affiliate foreign company with the objective of producing export commodities."

https://t.me/customsclearingagents

፯/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል፡-

"፪/ አምራቹ በምርት ሒደት ውስጥ በባከነው ጥሬ ዕቃ እና ተረፈ ምርት ላይ አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተገቢውን ቀረጥና ታክስ በመክፈል የባከነውን ጥሬ ዕቃ እና ተረፈ ምርት ሀገር ውስጥ መሸጥ ይችላል፡፡"

7/ Sub-Article (2) of Article 23 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new Sub-Article (2):

"2/ The producer may, against payment of the taxes and duties under the applicable law, sell in local market the raw materials wasted in the process of production and the byproducts."

፰/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፬ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፳፭ ተተክቷል፡-

8/ Article 24 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new Article 25:

"፳፭. <u>ቀረጥ ያልተከፈለባቸውን ጥሬ እቃዎች ወይም ምርቶች አጠቃቀም የጊዜ ገደብ ስለማራዘም</u>

የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለባቸው ጥሬ ዕቃዎች ወይም ምርቶች በዚህ አዋጅ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቅም ላይ መዋል ካልቻሉ ወይም ጥቅም ላይ ውለው ለውጭ ገበያ ካልተላኩ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፩ መሰረት ካልተላለፉ የጊዜ ገደቡን ማራዘም የሚቻልበትን ሥርዓት የሚወስን መመሪያ ያወጣል፡፡"

"25. <u>Extending the Time Limit for Using Raw Materials and Products Subject to Duty</u>

The Ethiopian Customs Commission shall issue directive to prescribe procedures of extending the time limit for exporting commodities produced by using raw materials or products or for transferring them in accordance with Article 21 of this Proclamation."

፱/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፯ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፳፰ ተተክቷል፡፡

9/ Article 27 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new Article 28.

"፳፰. <u>ወደ ሀገር የገባን ሸቀጥ ወይም ጥሬ ዕቃ ወደ መጣበት ሀገር ስለመመለስ</u>

፩/ በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ቀረጥ ሳይከፈልባቸው ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ጥሬ ዕቃዎችና ምርቶች በግዥ ትዕዛዙ የተመለከተውን ስፔስፊኬሽን የማያሟሉ፣ የተበላሸ፣ የጐደሉ ወይም በገበያ ተፈላጊ የሆነ ምርት ሊመረትባቸው የማይችሉ ስለመሆኑ በሚመለከተው አካል የተረጋገጠ እንደሆነ ያለምንም ክፍያ ተጠቃሚው ወደ መጡበት ሀገር ተመልሰው እንዲወጡ ያደርጋል፡፡"

"28. <u>Re-exporting Raw Materials or Commodities to the Country of Origin</u>

1/ When the raw materials or commodities imported without payment of duty for use in the production of export commodity under the export trade duty incentives schemes are confirmed by the appropriate body be not in conformity with the purchase order specifications, damaged or which are in short delivery or which are not fit for use in the production of commodities in market demand may be re-exported to their

https://t.me/customsclearingagents

፪/ የ ዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ በሌሎች ሁኔታዎች ተጠቃሚው ጥሬ ዕቃዎቹን ወደመጡበት ሀገር መልሶ መላክ የሚችለው ሳይከፈል የቀረውን ቀረጥ ፭ በመቶ በመክፈል ነው።

፫/ በተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት የገቡ ከሆነ ግን በተመለሰው ጥሬ ዕቃ ወይም ምርት መጠን ተሰልቶ ከተከፈለው ቀረጥ ላይ ፺፭ በመቶ ይመለሳል።

2/ Subject to Sub Article (1) of this Article in other cases, the beneficiary can send the raw materials back to the country of origin by paying 5 percent of the unpaid duty.

3/ However, if the raw materials have entered through duty-drawback system, 95 percent of the tax paid will be returned based on the amount of the re-exported raw material or product.

፫. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በዚህ አዋጅ ከተሸፈኑ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶች አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ውሳኔ የወጣባቸው፣ በአቤቱታ አጣሪ ተቋማት የሚገኙ እና ሌሎች ፍፃሜ ያላገኙ ጉዳዮች በዚህ አዋጅ መሠረት ፍፃሜ ያገኛሉ።

3. Transitory Provisions

All pending cases in connection with the implementation of the tax incentive schemes covered by this Proclamation before the coming into force of this Proclamation including cases for which an assessment has been issued or cases that are pending before complaint handling institutions shall be resolved in accordance with this Proclamation.

፬. አዋጁ የሚጸናበት ቀን

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

4. Effective Date

This Proclamation shall come into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

አዲስ አበባ ነሐሴ ፳ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

ሣህለ ወርቅ ዘውዴ
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

Done at Addis Ababa, On this 14th Day of August, 2024
SAHLE WORK ZEWDIE
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

https://t.me/customsclearingagents